Global Alliance for Justice – The Ethiopian Cause: 4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044, USA: Tel: (214)703 9022

Email:info@globalallianceforethiopia.com; www.globalallianceforethiopia.org

መስከረም 24 ቀን 2006 ዓ/ም

ለክቡር አምባሳደር ዓለማየሁ አበበ
አዲስ አበባ።

**የምሥጋና ደብዳቤ፤**

እ.ኤ.አ በ1935-41 ፋሺሽት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ በፈጸመችው እጅግ አሰቃቂና የከፋ የሰው እልቂት እንዲሁም የንብረትና የአካባቢ ውድመት፤ በፖፕ ፓየስ 11ኛ የተመራችው የቫቲካን መንግሥት ከፋሺሽቶቹ ጋር እጅና ጓንት በመሆን የተፈጸመው የጦር ወንጀል በታሪክ ማስረጃ የተረጋገጠ ሐቅ በመሆኑ፤ ዓለም-አቀፍ ሕብረት ለፍትሕ - የኢትዮጵያ ጉዳይ የተሰኘው ማሕበራችን፤ ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ ያቀረበውን አቤቱታ በመደገፍ፤ ክቡርነትዎም ለፖፕ ፍራንሲስ 1ኛ የጻፉትን ግልጽ ደብዳቤ ተመልክተነዋል።

ለውድ ሐገራችን ለኢትዮጵያ ስለሚያስፈልገው ፍትሕ የበኩልዎን ግሩም በሆነው ደብዳቤዎ ጉዳዩን ስላጠናከሩት ጥልቅ ምሥጋናችንን እናቀርባለን። በዚህ አጋጣሚም፤ የተከበሩ የጀግኖች አባትዎን፤ የደጃዝማች አበበ ሽንቁጥንና የአጎቶችዎን መስዋእትነት በታላቅ አክብሮትና አድናቆት እናስታውሳለን። ከቀድሞ የኢትዮጵያ አምባሳደርና የጀግና ልጅ የሚጠበቀውን በማከናወንዎ ልባዊ ምሥጋናችንን እንገልጽልዎታለን።

ከማክበር ሰላምታ ጋር፤

ኪዳኔ ዓለማየሁ
ዋና ሥራ አስኪያጅ።